# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

ቁጥር 114 ሐምሌ 15 ቀን 2002 ገጽ 1

አንብበው ያስነብቡ! አባዝተው ያሰራጩ!

ግዜ
ግንቦት 7 ዜና

**የወቅቱ የግንቦት 7 የትግል ጥሪ**

**“የጋራ ውርደት እንዲያከትም እብሪተኞችን በጋራ እምቢ እንበል፤ ዘረኛውና አዋራጁን የወያኔ ስርዓት ለማስወገድ በጋራ እንነሳ!!!:”**

**ጥርሱን አግጦ ለወጣ የአምባገነኖች የምርጫ ለበጣ ምላሹ “እምቢ ለመብቴ!!!” ብቻ ነው**

## ዘረኛው የወያኔ አገዛዝ ህዝባችን አንድ ወጥ አመለካከት እንዲኖረው ለማድረግ የጀመረውን ዘመቻ ገፍቶበታል

ዘረኛውና አምባገነናዊው የወያኔ አገዛዝ የስልጣን ዕድሜውን ለማራዘም እንዲያስችለው ኢትዮጵያውያን ስለ አገዛዝ ሥርአቱ የልማት መንግሥትነት አንድ አይነት አመለካከት እንዲኖራቸው ለማድረግ የሚያካሄደውን ዘመቻ አጧጡፎ እንደቀጠለበት ከሰሞኑ ለዝግጅት ክፍላችን የሚደርሱ ዘገባዎች አሳይተዋል።

ዘረኛውና ነፍሰ ገዳዩ መለስ ዜናዊ ከበርካታ አመታት በፊት፣ የሚመራው ፓርቲ አላማ ኢትዮጵያውያን አንድ አይነት አመለካከት ኖሯቸው የአገዛዙን ፈቃድ ከማይቃወሙበት ደረጃ ላይ እንዲደርሱ ማድረግ ነው ሲል መናገሩን ከዚህ ቀደም መጥቀሳችን ይታወሳል። በዚህም አኳኋን ወያኔ በህዝባችን መተፋቱን ካወቀበት የምርጫ 97 ወዲህ ላለፉት አምስት አመታት ቁጥሩ በውል የማይታወቅ ከፍተኛ የአገር ሃብትና ገንዘብ በማፍሰስ ህዝቡ አብዮታዊ ዴሞክራሲን እንዲቀበል ዘርፈ ብዙ ዘመቻ ሲያደርግ መቆየቱ ይታወቃል።

ይህ ዘመቻ ከለፈው ግንቦት 15ቱ የምርጫ ተውኔት በኋላም ቀጥሎ በመቶዎች የሚቆጠሩ መምህራን የሙያ ስልጠና ይሰጣችኋል ተብለው ተሰብስበው ለአስራ አምስት ቀናት ስለ አብዮታዊ ዴሞክራሲ መሰበካቸውን ባለፈው ሳምንት መዘገባችን ይታወሳል። የግንቦት 7 ድምጽ ሪፖርተር በዚህ ሳምንት ከአዲስ አበባ አጠናቅሮ የላከው ዘገባ ደግሞ፥ ሰሞኑን በሙያ ስልጠና ስም የተሰበሰቡ የመንግስት ኦዲተሮች ተመሳሳይ እጣ እንደገጠማቸው አሳይቷል። (ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

## በኢትዮጵያ ያለው የዘውግ ፌዴራሊዝም ለወያኔ ዘረኛ አገዛዝ መደበቂያ ሽፋን ነው ሲሉ አንድ ፈረንሳዊ ጸሃፊ ገለጹ

ረኔ ለፎ የተባሉ እና ላለፉት 40 አመታት በአፍሪካ ጉዳዮች ላይ ሲጽፉ የቆዩ ፈረንሳዊ ጋዜጠኛና ጸሃፊ በዚህ ሳምንት ባወጡት ጽሁፍ፣ በኢትዮጵያ ሰፍኖ ያለው በዘውግ ላይ የተመሰረተ ፌዴራሊዝም በአገሪቱ ውስጥ ላለው ዘረኛ ስርአት እንደ ሽፋን ሆኖ የሚያገለግል ነው ሲሉ መስከረዋል።

ከኢትዮጵያ ህዝብ ስድስት በመቶ የሚሆነውን የሚወክሉት የትግራይ ተወላጆች በኢትዮጵያ ውስጥ ስልጣንን እና ሁሉንም የኢኮኖሚ ዘርፎች ተቆጣጥረው እንዳሉ ጸሃፊው ገልጸዋል።

የግንቦት 7 ድምጽ በተለያዩ ጊዜያት ባወጣቸው ጥናታዊ ጽሁፎች እና ዘገባዎች የወያኔን ዘረኛነት ሲያጋልጥ እና ሲያወግዝ መቆየቱ ይታወቃል።

ረኔ ለፎ በዚሁ ጽሁፋቸው ላይ፥ አገዛዙ የትግራውያን የበላይነት እንዲቀጥል መስራቱ እውነተኛ ዴሞክራሲ በአገሪቱ ውስጥ እንዳይኖር እንዳደረገ እና ለአገሪቱ አለመረጋጋትም ዋና ምክንያት እንደሆነ ተናግረዋል።

## የኢትዮጵያ ዋና ዋና ከተሞች በከፍተኛ ጥበቃ ስር መሆን የአገዛዙን በራስ ያለመተማመን ያሳያል ተባለ

ዘረኛውና አምባገነናዊው የወያኔ አገዛዝ በአንዳንድ የአገሪቱ ዋና ዋና ከተሞች ከፍተኛ ጥበቃ እያካሄደ መሆኑን ሰሞኑን የደረሰን ዘገባ አመልክቷል።

የግንቦት 7 ድምጽ ዘጋቢ ከሰሜን ኢትዮጵያ አጠናቅሮ በላከው መረጃ መሰረት በባህር ዳር፣ በጎንደር፣ እና በደሴ ከተሞች ፖሊሶች በየ100 ሜትር እንዲቀመጡ ከመደረጋቸው በተጨማሪ የፌዴራል ፖሊሶች፣ የመከላከያ እና ልዩ ሃይል ወታደሮች በከተሞቹ ተሰማርተዋል። እንደ ሪፖርተራችን ገለፃ፥ ጠብመንጃ ታጥቀው የሚዘዋወሩት ፖሊሶች እና ወታደሮች ከተሞቹን የጦር ቀጠና አስመስለዋቸዋል።

ጉዳዩን በሚመለከት ዘጋቢያችን ያናገራቸው ግለሰብ ይህ አገዛዙ ስጋት እንዳለበት እንደሚያሳያቸው ገልጸዋል። ግለሰቡ ጨምረው፥ ወያኔ በግንቦት 15ቱ ምርጫ ከራሱ ጋር ተወዳድሮ የፓርላማውን መቀመጫ ሙሉ በሙሉ ቢቆጣጠርም በራስ መተማመን እንደሌለው አመላካች ነው ብለዋል።

## ዘረኛውና አምባገነናዊው የወያኔ አገዛዝ በአፋር በተነኮሰው ግጭት በርካቶች ሞተዋል ተባለ

ዘረኛውና አምባገነናዊው የወያኔ አገዛዝ በአፋር ክልል በሚተነኩሰው ግጭት በርካቶች እየተገደሉ ነው ሲል የአፋር ህዝብ ፓርቲ በለቀቀው መግለጫ አስታወቀ።

በቅርቡ ባዱ በሚባል አካባቢ በተከሰተ ግጭት 30 ሰዎች ሞተው 50 የሚሆኑ ሴቶች፣ ህፃናት እና አዛውንቶች መቁሰላቸውን ፓርቲው ገልጿል። ከሁለት ወራት በፊትም በክልሉ የጋዋኔ ወረዳ አስተዳዳሪ የሆነው ግለሰብ ባልታወቁ ሰዎች መገደሉ ታውቋል። የአካባቢው ነዋሪዎች ወያኔ የእርስበርስ ግጭት ለመተንኮስ እና የግንቦቱን ምርጫ የተቃወሙ ተቃዋሚ ፓርቲዎችን መምቻ ምክንያት ለማግኘት ሲል ሆን ብሎ የፈጸመው ትንኮሳ ነው ብለው እንደሚያምኑ መግለጫው ይናገራል። በአሁኑ ወቅት 20 የሚሆኑ የተቃዋሚ ፓርቲ አባላት እና የሃገር ሽማግሌዎች በእስር ላይ እንደሚገኙም ታውቋል።

መግለጫው የወያኔ እኩይ ተግባር የመነጨው አገዛዙ የክልሉን መሬት ለመቆጣጠር እና ከሱ ጋር ትስስር ላላቸው ነጋዴዎች ለመስጠት እያካሄደ ካለው ሩጫ ነው ብሏል። ከብቶች በማርባት የሚተዳደረው ህዝብ ለከብቶቹ ግጦሽነት ይጠቀመው ከነበረው መሬት ያለምንም ካሳ እየተፈናቀለ እንደሆነ እና የአዋሽን ወንዝም መጠቀም የማይችልበት ደረጃ ላይ እንደደረሰም አትቷል። (ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

## በኡጋንዳ የሚገኙ ኢትዮጵያውያን ስደተኞች አጣብቂኝ ውስጥ መግባታቸው ተዘገበ

እሁድ ሐምሌ 4 ቀን በኡጋንዳ ዋና ከተማ ካምፓላ የደረሰው ፍንዳታ በአስርት የሚቆጠሩ ሰዎችን ከገደለ በኋላ በአገሪቱ የሚገኙ ኢትዮጵያውያን በጥርጣሬ አይን እየታዩ መሆናቸውን ዘገባዎች አሳይተዋል።

የፍንዳታው አደጋ ከደረሰባቸው ቦታዎች አንዱ የኢትዮጵያውያን ንብረት የሆነ ምግብ ቤት እንደሆነ መዘገቡ ይታወሳል። ከሟቾቹም ውስጥ አንዱ ኢትዮጵያዊ መሆኑ እስካሁን የተረጋገጠ ሲሆን፤ የቆሰሉም እንዳሉ የተለያዩ ዘገባዎች አሳይተዋል። ይሁን እንጂ የአሜሪካ ድምጽ ሪፖርተር ፒተር ሃይነላይን ከካምፓላ እንደዘገበው፥ በኡጋንዳ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን አጣብቂኝ ውስጥ ገብተዋል።

በአንድ በኩል የኢትዮጵያውያን ምግብ ቤት የተጠቃበት ምክንያት የወያኔ ጦር የሶማሊያን የሽግግር መንግስት በመርዳት በአገሪቱ ያደረገውን ጣልቃ ገብነት እንደ አልሸባብ ያሉ ቡድኖች ኢትዮጵያውያንን በያሉበት በማጥቃት ለመበቀል በመፈለጋቸው ነው ተብሎ ይታመናል። በሌላ ጎን ደግሞ ከዚህ ቀደም በመልካም እንግዳ ተቀባይነት በተንከባከባቸው የኡጋንዳ ህዝብ ፊት በጥርጣሬ አይን መታየት ጀምረዋል። ይህ ሊሆን የቻለበትን ምክንያት (ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

## ፓትሪያርክ አቡነ ጳውሎስ በቦሌ መድሃኔአለም ቤተክርስቲያን ፊት ለፊት ለራሳቸው ያስገነቡት ሃውልት አነጋጋሪ ሆኖ ሰነበተ

በአዲስ አበባ የሚገኙ አድባራትና ገዳማት የፓትሪያርክ አቡነ ጳውሎስን 18ኛ ዓመት በዓለ ሲመት ምክንያት በማድረግ 3.4 ሚሊዮን ብር የሚያወጣ መኪና ሽልማት የሰጡ መሆናቸውን ደጀ ሰላም ኮም ድረ ገጽ ዘግቧል። ደጀሰላም እንደገለጸው ድርጊቱ ከአዲስ አበባ ሐገረ ስብከት ፈቃድ ውጭ በፓትሪያሪኩ ሰዎች መልካም ፈቃድ የተዘጋጀ ከመሆኑም ባሻገር የአድባራቱን አቅም ግምት ውስጥ ያላስገባና እንዲያዋጡ የተጠየቁትን ገንዘብ በምን አይነት ሁኔታ ከሚኖር ሕዝብ እንደሚሰበስቡት ያላገናዘበ መሆኑን አትቷል። ከዚሁ ጋር ተያይዞም ከዚህ በፊት ተደርጎ በማይታወቅ ሁኔታና የቤተክርስቲያኒቷን ህግና መመሪያ በጣሰ መልኩ ቦሌ በሚገኘው መድሃኔዓለም ቤተክርስቲያን ቅጽር ግቢ ውስጥ ለቅዱስነታቸው ማስታወሻ በሚል ለፓትሪያሪኩ ሐውልት እንዲቆም የተደረገ መሆኑን አክሎ ገልጿል።

ዜናውን ተከትሎ የተለያዩ ግለሰቦች ድረገጹ ላይ በሰጡት አስተያየት ለሐውልቱ የወጣውን ወጭ እና ሊተላለፍ የተፈለገው መልእክት ሲታሰብ ቤተክርስቲያኒቷ ምን ያህል ከሐይማኖታዊ ጥንተ መሰረቷና ተውፊቷ እርቃ እንደሄደች ያሳየናል፤ አንድ አባት እንኳንስ በህይወት እያለ ይቅርና በአጸደ ነፍስ ቢሆን እንኳ ሶስት ገጽ ያለው ምስል ለራሱ ማቆም ጣኦትን እንደማምለክ ስለሚያስቆጥር በጥብቅ የተከለከለ ነው ብለዋል። (ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

## በካምፓላ በደረሰው ጥቃት የተሰማንን ጥልቅ ሃዘን እንገልፃለን፤ በዚህ አጋጣሚም ኢትዮጵያዊያን የተሸከምነው ኃላፊነት ክብደት ይሰማን እንላለን

ግንቦት 7: የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ ሐምሌ 4 ቀን 2002 ዓ.ም. በኡጋንዳ ዋና ከተማ ካምፓላ በደረሰው የአጥፍቶ ጠፊዎች ጥቃት ሕይወታቸውን ላጡ፤ የአካልና የስነልቦና ጉዳት ለደረሰባቸው ወገኖቻችንና ቤተሰቦቻቸው የተሰማውን ጥልቅ ሃዘን ይገልፃል። ግንቦት 7 በዚህ ጥቃት ጉዳት የደረሰባቸውን የኡጋንዳና የሌሎች አገራት ዜጎችም ሃዘን ይጋራል። ንቅናቄዓችን ፓለቲካዊም ሆነ ሃይማኖታዊ ዓላማን ለማሳካት ሲባል በንፁሃን ዜጎች ላይ የሚደረግ ጭፍጨፋን አጥብቆ ያወግዛል።

በአገራችን በኢትዮጵያ ከተንሰራፋው ህገ-አልበኝነት እና ዘረኛ አገዛዝ በመሸሽ ሕይታቸውን ለማትረፍ የተሰደዱ ወገኖቻችን የጥቃቱ ዒላማ መሆናቸው ሃዘናችንን እጥፍ ድርብ አድርጎታል። ወያኔ በሶማሊያ ውስጥ ለተከተለው ጀብደኛ ፓሊሲ ምስኪን ኢትዮጵያዊያን ዋጋ መክፈላቸው እጅግ አሳዛኝ ጉዳይ ነው። የወያኔ ጀብደኝነት አገራችንን ከማትወጣበት አጣብቂኝ ውስጥ ሊከታት እንደሚችል በተደጋጋሚ ሲገለጽ የቆየው ምን ያህል እውነት እንደሆነ የሰሞኑ የካምፓላው አሳዛኝ ክስተት ግልጽ አድርጎልናል። ወያኔ ገና ለብዙ ዓመታት የምንዳክርበት የሶማሊያ ማጥ ውስጥ ከቶናል።

ከዓመታት በፊት የአካባቢው አገሮች በሶማሊያ ጉዳይ ጣልቃ ከመግባት እንዲታቀቡ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ያሳለፈው ውሳኔ በወያኔ ግንባር ቀደም አዝማችነት ከተጣሰ ወዲህ የሶማሊያ ሁኔታ እያደር እየባሰ ለአካባቢው አገሮች በሙሉ ፈተና እየሆነ መጥቷል። ወያኔ በሶማሊያ ጉዳይ አዛዥ ልሁን ባለ መጠን አፀፋው የከፋ እንደሚሆን፤ የሶማሊያ ለዘብተኛ ዜጎች ሳይቀሩ በኢትዮጵያ ላይ ቂም እንዲቋጥሩ መደረጉ በዓይናችን እያየነው ያለ ጉዳይ ነው። ይህ የወያኔ ጀብደኛ ጣልቃ ገብነት የሶማሊያ ችግር ተባብሶ ዓለም ዓቀፍ ገጽታ እንዲኖረው በማድረጉ እነሆ ዛሬ በጎረቤት አገር ጠለላ ሥር የሚገኙ ወንድሞቻችንና እህቶቻችን ሕይወት አደጋ ላይ ሊወድቅ ችሏል። ሶማሊያ የዘመተው የወያኔ ጦር የሶማሊያን የውስጥ ችግር እቤታችን ድረስ ጎትቶ ስላመጣዉ ችግሩ በዚህ የሚቆም አይመስልም። ሰሞኑን የወያኔ ወዳጅ ነኝ ባዩ የሼክ ሸሪፍ አህመድ አገዛዝ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ለግብፅ ጋዜጣ "ኦጋዴን ኢትዮጵያ የቀማችን የሶማሌ ግዛት ነዉ" ብሎ የተናገረውን ላስተዋለ ስጋታችን የበለጠ ይገባዋል ብለን እናምናለን።

የዓለም ዓቀፉ ኅብረተሰብም የወያኔ ዓይነቱ የወንበዴ ቡድን በሌላ አገር ሰላምና መልካም አስተዳደርን ያሰፍናል ብሎ መገመቱ አንድም የዋህነት አሊያም ግድየለሽነት ነው። አገሩን በዘር ከፋፍሎ እያመሰ ያለ ቡድን ቀድሞውኑ በዘር የተከፋፈለን የጎረቤት አገር ሕዝብ አስማምቶ መልካም አስተዳደር እንዲሰፍን ይረዳል ማለት ከእባብ እንቁላል እርግብን መጠበቅ ነው።

ግንቦት 7 የሶማሊያ ችግር አሳሳቢ እንደሆነ ይረዳል። በዚያው መጠን ደግሞ ወያኔ ሶማሊያን አስመልክቶ የተከተለውን ፖሊሲ አጥብቆ ይቃወማል። የሶማሊያ ችግር መፍትሄ የሚያገኘው በዋነኛነት በራሳቸው በሶማሊያውያን መሆን ይኖርበታል። ከዚህ በተጨማሪ በኢትዮጵያ ውስጥ በሕዝብ የተመረጠ መንግሥት መኖር ለአካባቢው ሁሉ ሰላም መሠረት እንደሆነ አስረግጠን እንናገራለን።

ኢትዮጵያን ለማዳን መረባረብ በአስከፊ ሁኔታ እየተበጠበጠ ላለው የአፍሪቃ ቀንድ ሰላም ዘላቂ መፍትሄ አስተማማኙ መንገድ ነው። ስለሆነም ኢትዮጵያዉያን የተሸከምነው ኃላፊነት ክብደቱ ሊሰማን ይገባል እንላለን።
ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!!!

**ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!!!**

### ፓትሪያርክ አቡነ ጳውሎስ በቦሌ መድሃኔአለም ቤተክርስቲያን . . .

(ከገጽ 1 የዞረ)

ከዚህ ቀደምም እነዚሁ የቤተክርስቲያን አባትና አስተዳዳሪ ነን ባዮች አቡነ ጳውሎስን ለማስደሰት በሚል በየአድባራቱ ትልልቅ ፎቶግራፎቻቸው እንዲሰቀሉ ማድረጋቸውና በአዲስ አበባ በሚገኙ አድባራትና ገዳማትም በያንዳንዳቸው ላይ 10000 ብር እንዲያዋጡ ማስገደጃ ተጥሎ እንደነበር ይታወሳል።

ከዚሁ ዜና ጋር በተያያዘ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ፓትሪያርክ አቡነ ጳውሎስ የአስራ ስምንተኛ አመት በአለ ሲመታቸውን ባከበሩበት እለት ለመታሰቢያቸው የተሰራው ሃውልት መመረቁን አስመልክቶ የወጣው ዜና ሰሞኑን በኦርቶዶክስ እምነት ተከታዮች ዘንድ አነጋጋሪ ሆኖ ሰንብቷል።

ለዝግጅት ክፍላችን ቃላቸውን የሰጡና ስማቸው እንዳይጠቀስ የሚፈልጉ የአዲስ አበባ ነዋሪ ይህንን ከሰሙ በኋላ ወደ ቤተክርስቲያን ላለመሄድ መወሰናቸውን ገልጸውልናል። እኒሁ ግለሰብ ከዚህ ቀደም በፓትሪያርኩ ላይ አሉታዊ አመለካከት ያልነበራቸውን ጨምሮ በርካታ የሚያውቋቸው ሰዎች በገንዘብ እጦት የተነሳ ጣሪያቸው የሚያፈስ ቤተክርስቲያኖች እና ብዙ ችግረኞች ባሉበት አገር ፓትሪያርኩ ለራሳችው ሃውልት ማስገንባታቸው አግባብ እንዳልሆነ በቁጣ ሲናገሩ መስማታቸውንም ተናግረዋል።

በተለያዩ ድረ-ገጾች ላይ ጉዳዩን በሚመለከት የተቃውሞ ጽሁፎች የወጡ ሲሆን፤ የአንባብያን አስተያየት መስጫ ሰሌዳዎቹም የቁጣ መግለጫዎች ሆነው ሰንብተዋል። ዳንኤል ክብረት የተባለው የቀድሞ የአዲስ ነገር ጋዜጣ አምደኛ እና "የሁለት ሃውልቶች ወግ" የተሰኘው መጽሃፍ ጸሃፊ፡- "ሰው በቁሙ ሐውልት ለምን ይሰራል?" በሚል ርእስ በድረ-ገጹ ላይ በለጠፈው ጽሁፍ፤ በህይወት ሳሉ ሐውልትን ለራሳቸው የሚያስገነቡ ሰዎች ከሞቱ በኋላ ለነሱ ሐውልት የሚያቆም እንደሌለ የሚያውቁ ናቸው ብሏል።

በጹፉ ስር አስተያየታቸውን ከጣሉት አንባቢዎች ውስጥ አቶ ደረጄ የተባሉ ግለሰብ፥ "ብዙ ጊዜ የቤተክርስቲያናችን የዶግማ እና ቀኖና ህጎች በመሪዎቻችን ሲሰበሩ አፎቻችንን ዘግተን ቆይተናል። እስከመቼስ ይቀጥላል? ይህንን ለማቆም የምንሰራበት ጊዜ አሁን ነው።" ብለዋል።

አቶ አዲሱ የተባሉት ግለሰብ ደግሞ፥ "እንኳን ፓትሪያርኩን እና አቡኑን ቀርቶ፣ ተራ አማኝ ሶስት ገጽ ያለው ሃውልት በቤተክርስቲያናችን ወግ እና ደምብ ውስጥ እንደማይደረግ ያውቃል። የቤተክርስቲያኒቱን ወግ እና ደንብ ማስጠበቅ ያለባቸው ፓትሪያርክ ግን ያንን ለመስበር የመጀመሪያው ሆነዋል።" ብለዋል።

ፓትሪያርክ አቡነ ጳውሎስ ከወያኔ ጋር ጥብቅ የሆነ የጥቅም እና የመንደር ልጅነት ትስስር እንዳላቸው እና ያንንም ተጠቅመው በሳቸው ላይ ሂስ የሚያቀርቡትን ዝም የማሰኘት ልምድ እንዳላቸው ከዚህ ቀደም በተደጋጋሚ መዘገባችን ይታወሳል።

### ዘረኛው የወያኔ አገዛዝ ህዝባችን አንድ ወጥ . . . (ከገጽ 1 የዞረ)

በተጨማሪም፥ በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ወጣቶች ለየማህበረሰቦቻቸው አገልግሎትን በመስጠት ስም በአገዛዙ እንደተሰበሰቡ የታወቀ ሲሆን፤ እውነተኛው ስራቸው ግን የገዢውን ፓርቲ ፖለቲካ መግፋት እና በአገሪቱ ውስጥ ልማት እንዳለ ህዝቡን ለማሳመን መጣር እንደሆነ ዘገባው ገልጿል። ከወጣቶቹ ውስጥ የገዢው ፓርቲ አባላት የሆኑት ለዚህ አገልግሎታቸው እንደሚከፈላቸውም መረጃው ያስረዳል። ወያኔ ከምርጫ 97 በፊት 700 000ብቻ የነበሩትን አባላቶቹን ቁጥር በግዴታ ምልመላ 5 ሚሊዮን ማድረሱን በተለያዩ አጋጣሚዎች በመመስከር ላይ ይገኛል።

### ዘረኛውና አምባገነናዊው የወያኔ አገዛዝ በአፋር . . . (ከገጽ 1 የዞረ)

የአፋር ህዝብ ፓርቲ፥ ወያኔ እንደ ፈረንጆች አቆጣጠር በ1976 ባወጣው ማኒፌስቶ የአፋርን ክልል ከትግራይ ጋር የማዳበል እቅድ እንዳለው መግለጹን እና አሁን እየሰራ ያለው ስራም ያንን ለመተግበር የሚያደርገው ዝግጅት አካል ነው ብሏል።

ፓርቲው የአፋር ሽማግሌዎች በአንድነት በመቆም የህዝባቸውን አንድነት እንዲጠብቁ፤ ወጣቶችም ለፍትህ እና እውነት እንዲቆሙ፤ እንዲሁም ሌሎች ኢትዮጵያውያን ከአፋር ወንድሞችና እህቶቻቸው ጎን እንዲሰለፉ ጥሪ አቅርቧል። አለማቀፍ የሰብአዊ መብት ድርጅቶች በክልሉ ውስጥ ግጭቶች እየተካሄዱ ላሉባቸው ቦታዎች ትኩረታቸውን እንዲሰጡ እና አዲስ አበባ የሚገኙ የውጭ አገራት ኤምባሲዎችም ጉዳዩን እንዲመለከቱት ጥሪ አቅርቧል።

### በኡጋንዳ የሚገኙ ኢትዮጵያውያን ስደተኞች . . . (ከገጽ 1 የዞረ)

ዘገባው ሲገልጽም፣ ለጥቃቱ ሃላፊነቱን የወሰደው የሶማሊያው አልሸባብ እንደመሆኑ ሶማሊዎች በጥርጣሬ መታየት ጀምረዋል። ለብዙ ኡጋንዳውያን ደግሞ፥ ኢትዮጵያውያን፣ ኤርትራውያን እና ሶማሊዎች ስለሚመሳሰሉ አንዱን ከሌላው መለየት አስቸጋሪ ነው።

ፍንዳታውን አስመልክቶ ከካምፓላ ለአውራምባ ታይምስ ጋዜጣ ቃለ መጠይቅ የሰጠው የቀድሞ አዲስ ነገር ጋዜጣ አዘጋጅ አቶ ተስፋለም ወልደየስ በዚህ ምክንያት አንድ ኤርትራዊ በድብደባ መገደሉን ገልጿል። በኡጋንዳ ከሚኖሩ ኢትዮጵያውያን አብዛኞቹ የፖለቲካ እና የኢኮኖሚ ስደተኞች እንደሆኑ ይነገራል። እስካሁን ከፍንዳታው ጋር በተያያዘ ተጠርጥረው አራት ኢትዮጵያውያን መታሰራቸው የተዘገበ ሲሆን፤ ሊፈቱ እንደሚችሉ ፍንጮች እንዳሉ የኢትዮጵያውያን ማህበረሰብ ተወካዮች መግለጻቸውን የአሜሪካ ድምጽ ዘግቧል።

በግንቦት 7 የፍትህ የነጻነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ የህዝብ ግንኙነትና ቅስቀሳ ዘርፍ በሳምንት አንዴ የሚዘጋጅ ድርጅታዊ ልሳን

የፖስታሳጥን ቁጥር :- POBox: 4916
2003EX Haarlem, The Netherlands

# እየደመቀ የመጣው የሕዝብ የተባበሩ እሪታና ሊሰጠው የሚገባ ምላሽ

**በግንቦት 7: የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ የጥናትና ምርምር ኮሚቴ የተዘጋጀ: ሐምሌ 2002 (ክፍል 3)**

### 4. በሌሎቸ አገራት ከነበሩ ኅብረቶችና ጥምረቶች ምን እንማራለን?

በታሪክ ውስጥ የሚጠቀሱ አንዳንድ ትብብሮችና ጥምረቶች ለማመን የሚቸግሩ ውጤቶችን አስገኝተዋል። በአንዳንድ ሁኔታዎች በመሣሪያ ሊገኝ ከሚችል ድል በላይ በተቃዋሚ ድርጅቶች ተባብሮ መቆም ብቻ ሊገኝ ይችላል። ለምሳሌ ያህል የምከተሉትን ማንሳት ይቻላል።

4.1 በእንግሊዝ በ1688-1689፤ በስዊድን በ1909 በፍላጎትም በርዕዮተ-ዓለምም የማይቀራረቡ የመሳፍንትና የቡርዧ ቡድኖች ተደራድረው በፈረንሳይ የፈነዳውን ዓይነት ማኅበራዊ ነውጥ ሳያስፈልግ ለሥርዓት ለውጥ በቅተዋል።

4.2 በኮሎሚቢያ 1957-1958 ተቃዋሚ ፓርቲዎች ኅብረት ፈጥረው በመፈርጠማቸው የተደናገጠው በሥልጣን ላይ የነበረውን ቡድን ግማሽ የመንግሥት ሥልጣኑን በመልቀቅ የፕሬዚዳንትነት ሥልጣን ከተቃዋሚዎች ኅብረት ጋር በፈረቃ ሊለዋጥ ተስማምቷል።

4.3 በተመሳሳይ ሁኔታም በቬንዙዌላ በ1958 ተቃዋሚዎች የፈጠሩት ሰፊ መሠረት ያለው ኅብረት ሥልጣን ያለውን ፓርቲ አርበድብዶ አነስተኛ በሆነ መስዋትነት ሥልጣኑን እንዲለቅ ማድረግ ችለዋል።

4.4 በ1989 የፓላንድ የሙያ ማኅበራትና ሌሎች የፓለቲካና ማኅበራዊ ስብስቦች በሙሉ "ከሶሊዳሪቲ" ጎን በመቆማቸው ኮሚኒስት ፓርቲው ራሱን ለማዳን እንዲደራደር ማስገደድ ችለዋል። በተመሳሳይ ጊዜ ተመሳሳይ ነገር በቼኮዝላባኪያ ውስጥም ተከስቷል።

4.5 በ1994 በደቡብ አፍሪካ በኤኤንሲ ግንባር ቀደም መሪነት የተካሄዱ ጥምረቶችና ድርድሮች እጅግ ውስብስብና አስደናቂ ጥበብ የተሞላባቸበው ነበሩ። በተለይም እነዚህን ድርድሮች በዝርዝር ማጥናት እኛ ለምንገኝበት ሁኔታ ከፍተኛ ፋይዳ አላቸው ብለን እናምናለን።

ከላይ የተዘረዘሩት እና የመሳለሉ ክስተቶች በጣም አልፎ አልፎ ብቻ የሚያጋጥሙ ብርቅየዎች ከመሆናቸም በላይ እያንዳንዱ ክስተት ከበርካታ ዓለም ዓቀፍ እና አገር ዓቀፍ ሁኔታዎች የተሳሰሩ ነበሩ። ስለሆነም አንዳቸውንም መድገም አይቻል ይሆናል፤ ሆኖም ግን እያንዳንዱ ምሳሌ የአብሮ መቆምን ጉልበት አጉልተው ያሳያሉ።

### 5. ከራሳቸን ያልተሳኩ የትብብርና ጥምረት ሙከራዎች ምን እንማራለን?

### 5.1 *እንደ መንደርደሪያ*

በአገራቸን ታሪክ በፖለቲካ መስኩ የተደረጉ ብዙ የመተባበር ሙከራዎች አሉ። እነዚህን ሙከራዎች በሶስት አይነት መክፈል ይቻላል። የመጀመሪያው አንድ ተጽእኖ ማድረግ በሚችል ድርጅት ዙሪያ የተወሰነ የራሳቸው ነፃነት ያላቸው ነገር ግን አቅማቸው ደካማ የሆኑ ድርጅቶች የፈጠሩት ትብብር ነው። ሁለተኛው አቅማቸው ተመጣጣኝ የሆኑና ተመጣጣኝ ያልሆኑ ነገር ግን አንዳቸው በሌላው ላይ ተጽእኖ ማድረግ የማይችሉ የነፃ ድርጅቶች ትብብር ነው። ሶስተኛው አንድ ጠንካራ ድርጅት ምንም ዓይነት ነፃነት የሌላቸውን ድርጅቶች በማሰባሰብ ፈጠርኩ የሚለው ትብብር ነው።

ለመጀመሪያው ዓይነት ትብብር በደርግ/ሰደድና በሌሎቹ ኢማሌድህ በተሰኘው ስብስብ ውስጥ አባል በነበሩት ድርጅቶች መሃል ተፈጥሮ የነበረው ኅብረት ምሳሌ መሆን ይችላል። ለሁለተኛው አይነት ትብብር ምሳሌ መሆን የሚችሉት ወያኔ ስልጣን ላይ ከወጣ በኋላ ወያኔን ለመቃወም ተቋቁመው የነበሩትን ትብብሮች ይመለከታል። የአማራጭ ኃይሎች ምክር ቤት፣ የኢትዮጵያ ተቃዋሚ ፖለቲካ ድርጅቶች ሕብረት (ኢተፖድሕ)፣ የኢትዮጵያ ዲሞክራሲያዊ ኃይሎች ሕብረት (ኢዲኃሕ)፣ ቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ (ቅንጅት)፣ ትብብር ለነፃነትና ለዴሞክራሲ በሚል ስያሜ የሚታወቁት ትብብሮች የሁለተኛው ዓይነት ትብብር አገራዊ ምሳሌዎች ናቸው። ሶስተኛው አይነት ትብብር በስሙ ካልሆነ በስተቀር በመሠረቱ ትብብር አይደልም። ለእንዲህ አይነቱ "ትብብር" ጥሩ ምሳሌ የሚሆነው በወያኔ የሚዘወረው ኢህአዴግ ነው።

እነዚህ የትብብር ሙከራዎች በሙሉ በአንድ ወይም በሌላ ምክንያት ሊሳኩ አልቻሉም። የወያኔው ኢህአዴግ ዓይነቱ ትብብር መጀመሪያውኑ ሲታሰብ ወያኔ የራሱን ጡንቻ ካፈረጠመ በኋላ ለረጅም ግዜ ታጥሮ ከኖረበት ትግራይና የትግራይ ሪፐብሊክ ምስረታ ህልሙን በጉያው ሸጉጦ ወደ መሃል አገር ለመገስገስ ያለውን እቅድ ተግባራዊ ለማድረግ ሲል እራሱ ጠፍጠፎ ከፈጠራቸው ድርጅቶች ጋር የተመሰረተ በመሆኑ ትብብር ከሚለው ጎራ መመደቡ ተገቢ አይደለም ይባል ይሆናል፤ ይህ አባባል እውነት ነው። ይሁን እንጂ በኅብረት ስም እንደምን ያህል ነውር እና ወንጀል መፈጸም እንደሚቻል ኢህአዴግ ምሳሌ በመሆኑ እዚህ ላይ መጠቀሱ ተገቢ ነው እንላለን።

የወያኔ የባህል ዝንባሌ ሃገር በቀል በመሆኑ ሌሎችም ድርጅቶች ቢሆኑም ለብቻቸው ስልጣን መያዝ ባይችሉ፣ አቅሙና ሁኔታው እስከፈቀደላቸው ድረስ ነፃና እኩያቸው ከሆኑ ድርጅቶች ጋር እውነተኛ ትብብር ከማድረግ ይልቅ በድብቅ ራሳቸው ከፈለፈሏቸው ወይም ከሚቆጣጠሯቸው ድርጅቶች ጋር ትብብር አደረግን ማለት የሚመቻቸው ለመሆኑ ጠቋሚ ነው። ትብብር የሚደረገው ልዩነት ባላቸው ኃይሎች መሃከል ያለውን ቅራኔ አስወግዶ ለሁሉም የሚመች መንገድ ለመፈለግ መሆን ሲገባው የተለጣፊ ድርጅቶች "ትብብር" በመፍጠር የራስን አጀንዳ በሌሎች ችከሻ ማስፈፀም በመጨረሻ ለብልጣብልጡ ድርጅት ሳይቀር ችግር እንደሚፈጥር ከወያኔ የጥፋት ታሪክ መማር ተገቢ ነው። "ኢህአዴግ" እያለ ወያኔ የሚጠራውን የወሮበሎች ተቋምን በትብብር ምሳሌነቱ ማንሳት ተገቢ የመሰለንም በተመሳሳይ መንገድ ትብብርን ለአንድ ድርጅት ጠባብ ዓላማ የማዋል ዝንባሌ ከወያኔም ውጭ ይኖራል ብለን ስለምናምን ነው።

የኢማሌድህ ትብብር በሰደድ አሸናፊነት መጠናቀቁ ብዙም ሊገርመን አይገባም። የትብብሩ ዓላማ የመድበለ ፓርቲ የፖለቲካ ሥርዓት ለመፍጠር ሳይሆን የሠራተኛውና የአርሶ አደሩን ጥቅም የሚያስከብር አንድ ሶሻሊስት ፓርቲ መመስረት ስለነበር ሰደድ ሁሉንም ጨፍለቆ የኢትዮጵያ ሠራተኞች ፓርቲ (ኢሠፓ) ብቸኛ ጌታ ሆኗል። በዚህ ምሳሌም ውስጥም ቢሆን ጠቃሚ ትምህርት የለም ማለት አይደልም። ሥርዓቱ የሚያዘው በአንድ አገር አንድ ፓርቲ ብቻ እንዲኖር ቢሆንም በጋራ ለዚህ ፓርቲ መመስረት መሰባብ የጀመሩ ድርጅቶች እርስ በርስ ሳይባሉ ተከባብረወና ተስማምተው ራሳቸውን አንድ ማድረግ አለመቻላቸው ራሱ የሚሰጠን ትምህርት አለ። እንዲህ አይነቱ መጠፋፋት የርዕዮተ-ዓለም ልዩነት በሌላቸው ድርጅቶች መካከል ሊፈጸም ከቻለ የርዕዮተ-ዓለም ልዩነት አለን በሚሉና የየራሳቸውን አደረጃጀት ይዘው በሚንቀሳቀሱ ድርጅቶች መካከል በመከባበርና በስምምነት ላይ የተመሰረተ የትግል ኅብረት ለመፍጠር የሚኖረውን ችግር ጥልቀት መረዳት አያስቸግርም። **ይህ እውነታ የሚያሳየን በኢትዮጵያ ውስጥ በጋራ ለመስራት የሚደረጉ ጥረቶች እንዲሳኩ የድርጅቶች የዓላማና የፖሊሲዎች ተመሳሳይነት ብቻውን በቂ እንደማይሆን ነው።**

ወያኔ ስልጣን ላይ ከወጣ በኋላም የተደረጉ በርካታ ተባብሮ የመስራት ሙከራዎች መሰናከል ምክንያቶች እንደ ትብብሮቹ ሁሉ በርካታ ናቸው። ችግራችን ግን በዋንኛነት ስለ ወያኔ ምንነትና ማነነት፣ ወይም በተለያዩ ፖሊሲዎች ላይ ካለን ልዩነት የመጣ አይደለም። ኢማሌድህ ውስጥ ሰደድ ሁሉንም ውጦ ኮሎኔል መንግሥቱ ኃይለማርያምን ብቸኛ አዛዥ እንዳደረገ ሁሉ፤ ወያኔም ተለጣፊዎቹን አሰባስቦ የመለስ ዜናዊ የግል ተላላኪ አድርጎ እንዳሰማራ ሁሉ፤ ግላዊና ማኅበራዊ ስነልቦናችን እንዲሁም ባህላችን ሁሉንም ጠቅልሎ ለመቆጣጠር ፍላጎት ያላችው የፖለቲካ ሰዎችን የሚያመርት መሆኑ ከወያኔ በኋላ ለተሞከሩት ትብብሮች ውድቀት ዋነኛው ምክንያት ነው። የፖለቲካ ሰዎች ለላቀ አገራዊና ሕዝባዊ ጠቀሜታ ሲሉ እኔ ብቻ ያልኩት ካልሆነ፣ የኔ ድርጅት ይህንን ስልጣን በትብብሩ ውስጥ ካልተሰጠው፣ የኔ ድርጅት የተለየ ጠቀሜታ ካላገኘ በሚሉ ድብቅ ፍላጎቶች የሚነሱ ተግባራትን መቆጣጠር ባለመቻላቸው እነዚህ ትብብሮች ለመፍረስ ችለዋል። ምክንያቶቹ ግን እነዚህ ብቻ ናቸው ግን ማለት አይደለም።

ከወያኔ ስልጣን ላይ መውጣት በኋላ ለተሞከሩ የትብብር ምስረታዎች መክሸፍ ኋላቀር አመለካከታችን ያሳደረውን ተጽዕኖ የሚያሳዩ ሌሎችን በማስረጃ የተደገፉ በርካታ ምሳሌዎች ማቅረብ ይቻላል። ሆኖም ክርክራችንን በማስረጃ ብናስደግፍም እንኳን በግለሰቦችና በድርጅቶች ላይ የተሰንዘረ ጥቃት መስሎ ስለሚታይ ሊፈጠር ይገባል ብለን ለምናልመው አዲስ የትብብር ጅማሮ እንቅፋት ይሆናል በሚል ስጋት በዝርዝር ልንገባበት አንሻም። ስለሆነም እገሌን ከእገሌ ባልለየ መልኩ ጉድለቶቻችንን ለይተን በማየት ለወደፊቱ የሚሆን ትምህርት ለመቅሰም በሚያበቃን መጠን ብቻ ጥቂት ምሳሌዎችን እናነሳለን።

"ትብብርን" ተጠቅሞ የራስን ድርጅትና ሌሎችን በእኩልነትና በመግባባት ለማስተናገድ ፈቃደኛነቱ ያልታየባቸው ሁኔታዎች ለትብብር መፍረስ ምክንያት ሆነዋል። ትብብር የሚል ቃል ተጠቅሞ ሊተባበሩ ፍላጎቱን ባሳዩ ኃይሎች መካከል ከዚህ ቀደም የነበረ ግጭትና መቃቃር መልሶ ሕይወት እንዲዘራ በማድርግ በትብብሩ ውስጥ የተካተቱ ኃይሎችን በቂምና በጥላቻ ዓይን ማየት፣ የግለሰቦችንና የድርጅቶችን ስም በመርዘኛ ወሬና አሉባልታ ማጥፋት ሌላው ችግር ነው።

ትብብርና ቂም፣ ትብብርና ጥላቻ፣ ትብብርና ንቀት፣ ትብብርና ሸፍጥ፣ ትብብርና ግለኛነት አንድ ላይ ሊሄዱ አይችሉም። ያለን ምርጫ ከሁለት አንድ ብቻ ነው። እነዚህ ሁለት ምርጫዎች ወይ ቂማችንን፣ በቀለኛነታችንን ጥላቻቸንን፣ ንቀታችንን፣ ግለኛነታችንን ታቅፈን ሁላችንም በተናጠልና በጋራ መለስ ዜናዊን የመሰለ ፀረ-ኢትዮጵያ ዘረኛ አዋርዶና ቀጥቅጦ እንዲገዛን እና በብዙ መስዋዕትነት ቀድምቶቻችን ያኖሯትን ሃገር እንዳሻው እንዲዘርፍና እንዲያፈርስ መፍቀድ አልያም ለመተባበር እንቅፋት የሆኑትን ባህላዊና ስነልቦናዊ እንከኖች ከውስጣችን መጥርግና ለነፃነት፣ ለፍትህ፣ ለእኩልነትና ለአንድነት በጋራ መቆም ናቸው።

ያነሳነው ችግር ስር የሰደደ የባህል ችግር ነውና "እባካችሁ እናጥፋው" በሚል ሰበካ ብቻ ሊጠፋ እንደማይችል እናውቃለን። ነገር ግን ችግሩ እንዳለ እስካወቅን፣ በተለይ ችግሩ ሁላችንም ይመለከታል ብለን ለመፍትሄ ከጣርን እድሉን ካገኙ አገርን የመምራት ብቃት እንዳላቸው ለሚናገሩ የፖለቲካ መሪዎች የሚሳን ሊሆን አይገባውም። ሆኖም ግን ይህንን ችግር ለመቅረፍ ራሳቸንን እንመርምር ከሚል ተማጽኖ በላይ ተሻግረን ያለፉ ትብብሮችን ያሰናከሉ ችግሮች ደግመው እንዳይከሰቱ መዋቅራዊና መርሃዊ መከላከያዎችን ማስቀመጥ ይኖርብናል። ይህን ለማድረግም ሁኔታዎች ከመቼውም በላይ የተመቻቹ ናቸው። (ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## እየደመቀ የመጣው የሕዝብ የተባበሩ እሪታና . . .

(ከገጽ 1 የዞረ)

አዲሱ የፖለቲካ ግንዛቤ፣ በተለይ በዋንኛው የአገሪቱ የፖለቲካ ችግር ላይ ያለው ግንዛቤ ከተለያዩ ብዥታዎች ጠርቶ አንድ መስመር ይዟል። **የፖለቲካችን ችግር ሕዝብ የስልጣን ባለቤት እንዳይሆን ያገዱትን መሰናክሎችን የማስወገድ ችግር ነው።** በአሁኑ ወቅት ሕዝብ ዴሞክራሲያዊ ይሁንታ ሳይሰጣቸው በጉልበትም ሆነ በሸፍጥ ስልጣን መያዝ አለብን ወይም ይቻላል ብለው የሚያሰቡ ድርጅቶች ቁጥራቸው እየተመናመነ ነው። ይህ ስሜት ያላቸው ድርጅቶች ቢኖሩም ባለፉት ጥቂት ዓመታት ውስጥ በአገር ውስጥና ከአገራችን ውጭ በማኅበረተሰባችን ውስጥ ዴሞክራሲን በሚመለከት የተደረሰበት ግንዛቤና ለዴሞክራሲ ትግሉ የተከፈለው መስዋዕትነት የሚያነቃንቃቸው እንዳልሆነ ያውቁታል። አንዳቸውም በአደባባይ፣ ሕዝብ ፊት ቆመው ስልጣን በጉልበት ወይም ሕዝብን ባገለለ መልኩ በፖለቲካ ልሂቃኑ መካከል በሚደረስ የውስጥ ስምምነት መያዝ ይገባዋል ብለው መናገር ከማይችሉበት ደረጃ ላይ ደርሰናል። **ስልጣን ላይም ያለው አምባገነናዊ የወያኔ ድርጅት ሳይቀር ህጋዊነቱን ከዴሞክራሲ ጋር ለማያያዝ ሲተጣጠፍ እንጂ የስልጣኔ ምንጭ ከደደቢት በረሃ አንግቤ የመጣሁት ጠመንጃዬ ነው ብሎ ደፍሮ አይናገርም። ከእንግዲህ የዴሞክራሲን ጽንስ ሃሳብ የበላይነት በኢትዮጵያ ውስጥ ማንም ሊያስቆመው አይችልም።**

ከዚህም በተጨማሪም ምርጫ 2002ን ተከትሎ የመጣው እውነታ የፖለቲካ ድርጅቶችን ሆነ የማኅበረሳባችን ግንዛቤ ቀይሮታል። **ወያኔ ስልጣን ላይ እስካለ በምርጫ በሚደረግ የፖለቲካ ድርጅቶች ውድድር ሰላማዊና ዴሞክራሲያዊ የስልጣን ሽግግር እንደማይቻል ለሁሉም ግልጽ ሆኗል።** ይህ እውነታ ቀደም ብለው በነበሩ የትብብር ሙከራዎች ተከስተው የነበሩ ችግሮችን አሰወግዷቸዋል። ወያኔ ስልጣን ላይ ሆኖ በምርጫ ስልጣን መያዝ ይቻላል የሚል ቀቢጸ ተስፋ በነበረበት ወቅት በድርጀቶች መሃል የሚደረግ ትብብር ተቃዋሚዎቹ ስልጣን ቢይዙ በሥራ ላይ ለማዋል በሚፈልጓቸው በርካታ ፖሊሲዎች ላይ የጋራ አቋም ይዘው መገኘት የግድ ይላቸው ነበር። ይህ ማለት የኢኮኖሚ፣ ማኅበራዊ፣ አስተዳደራዊ፣ የውጭ ጉዳይና ሌሎችም ፖሊሲዎች ላይ የጋራ አቋም መያዝ ይገባቸው ነበር ማለት ነው። በኢትዮጵያ የፖለቲካ ድርጀቶች መካከል እንኳን በተጠቀሱት ፖሊሲዎች ዙሪያ ቀርቶ ከዛም ባነሱ ጉዳዮች ዙሪያ ስምምነት ላይ ደርሶ ትብብር መጀመርና የትብብሩን እድሜ ማራዘም ምን ያህል አስቸጋሪ ሊሆን እንደሚችል በተግባር ያየነው ነው።
ምርጫ 2002 ያደረገው ነገር የፖለቲካ ድርጅቶችን ለስልጣን ከሚደረገው ትግል በፊት ፊታቸውን ስልጣን በዲሞክራሲያዊ መንገድ ለመያዘ ወደሚቻልበት ትግል እንዲያዞሩ ማስገደድ ነው። በመሆኑም የፖለቲካ ድርጅቶች ቀደም ብለው በተጠቀሱት በበርካታ ፖሊሲዎች ዙሪያ ስምምነት ማድረግ ሳያስፈልጋቸው ለራሳቸውም ሆነ ለሕዘቡ የዴሞክራሲ መብቶች እንዲረጋገጡ በጋራ ትግል ለማድረግ የሚችሉብትን ሁኔታ ፈጥሯል። ከስልጣን መያዝ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ጉዳዮች ከትብብሩ ቀመር መወገዳቸው የመተባበር ሥራችንን አቅልሎታል።

ስልጣንን ለመጋራት የሚደረግ ትብብር እና ስልጣን በዲሞክራሲያዊ መንገድ የሚያዝበትን ሁኔታ በጋራ ለማመቻቸት የሚደርግ ትብብር ለየቅል ናቸው:: ስልጣን የሚያዘው በድርጅቶች መካከል በሚደረግ ድርድርና ትብብር ከሆነ "እኔ ስልጣን አነሰኝ፤ እከሌ ደግሞ በዝቶበታል" የሚል ጭቅጭቅ መቀስቀሱ አይቀሬ ነው። አንድ አይነት የትብብር ስምምነት ከተደረሰም በኋላም የሚገባኝን ስልጣን አላገኘሁም የሚል በሽታ ያገረሻል። ከፍተኛ ስልጣን በእጃቸው ይገባል ተብሎ የሚታሰቡ ግለሰቦችንና ድርጅቶችን መጠራጠር "አድብተው ጉድ ሊሰሩን ይችላሉ" ብሎ መስጋት ይኖራል። ይህ ጥርጣሬ በድርጅቶችና መሪዎች መካከል ያለውን መተማመን ገና ከመነሻው ያደፈርሳል።

ስልጣን የሚያዝበትን አግባብ ለማመቻቸት የሚደረገው ትብብር ግን ለእንዲህ ዓይነቱ ጥርጣሬ ሰፊ በር አይከፍትም። የ2002 የወያኔ የምርጫ መልዕክት ስልጣን በምርጫና በዴሞክራሲ ስም ከወያኔ መውሰድ የሚቻለው በወያኔ መቃብር ላይ መሆኑን ግልጽ ማድረጉ ለስልጣን የሚደረግን ትብብር ከፈረሱ የቀደመ ጋሪ አድርጎታል። ይህ እውነታ በማያጨቃጭቁ ጉዳዮች ዙሪያ እንድንተባበር መንገዱን ጠርጎልናል። ካለፉት የትብብር ውድቀቶቻችን ትምህርት መውሰድና ለነበሩት ችግሮች መፍትሄ መስጠት እንችላለን የሚል ድፍረት የሰጠንም የሁኔታዎች መቀየር ነው። ምን ማድረግ ይቻላል?

### 5.2 በባህል ረገድ ያለብንን ችግር በሚመለት

ባህልን በአጭር ጊዜ መቀየር አይቻልም። የባህል ለውጥ ረጅም ሂደት ነው። ሆኖም ግን ያ የለውጥ ሂደት መጀመር ይኖርበታል፤ መጀመር ያለብንም እኛው ነው። የሚከተሉትን ተግባራት በመከወን ረጅሙን የባህል ለውጥ አሁኑኑ መጀመር ይገባናል።

#### 5.2.1 በድርጅቶች የሚሰራ

- ከባህላችን የሚቀዱ ባለፈው ተባብሮ ለመስራት የተደረጉ ሙከራዎችን ያደናቀፉ ችግሮችን በመለየት በድርጅቶች መካከል መኖር ስለሚገባው የግንኙንት ስነ-ምግባር ዝርዝር መመሪያ ደንብ ማዘጋጀት፤
- በዚህ መመሪያና ደንብ መሰረት ሁሉም ድርጅቶች እንደሚገዙ በሕዝብ ፊት ቃልኪዳን እንዲገቡ ማድረግ፤
- ከባህልና በሌሎችም ጉዳዮች የሚነሱ ችግሮችን የሚሸመግል የግልግል ቦርድ ማቋቋም። በሽምግልና (በግልግል) እልባት ባላገኙ ጉዳዮች ላይ የመጨረሻ ውሳኔ የሚሰጥ ቦርድ ማቋቋም። በሚቋቋሙት ቦርዶች ውስጥ ሴቶችና ወጣቶች በቂ ውክልና እንዲኖራቸው ማድረግ። ቦርዶቹ ነጻና ገለልተኛ የፍትህ ተቋም በሚሰራበት መርህ እንዲደራጁና እንዲንቀሳቀሱ ማስቻል፤
- በዚህ ጉዳይ ላይ የተደረሰን የድርጀቶች ስምምነት ሁሉም ድርጀቶች ለአባላቶቻቸውና ለደጋፊዎቻቸው በሙሉ በእጃቸው በሚገኙ የመገናኛ አውታሮች ማስታወቃቸውን ማረጋገጥ፤
- በነፃ ሚድያዎች በጋራና በተናጠል በሚደረጉ ስብሰባዎች ይህንን የጋራ ስምምነት ለማኅብረተሰባችን ማሳወቅ፣ (ክፍል 4 ሳምንት ይቀጥላል)

## ዘጠና በመቶ የሚሆኑት ኢትዮጵያውያን ደሃ ናቸው ሲል በኦክስፎርድ ዩኒቨርሲቲ የወጣ ሪፖርት አስታወቀ

የኦክስፎርድ ዩኒቨርሲቲ አለማቀፍ ልማት ዲፓርትመንት አዲስ የድህነት መመዘኛን ስራ ላይ በማዋል ባካሄደው አሰሳ 90 በመቶ የሚሆኑት ኢትዮጵያውያን ድሆች እንደሆኑ ገልጿል።

"መልቲ ዳይሜንሺናል ፑቨርቲ ኢንዴክስ" ወይም ዘርፈ ብዙ የድህነት መመዘኛ የሚባለውን አዲስ ዘዴ በመጠቀም በተደረገው በዚህ ጥናት፣ ይህ በኢትዮጵያ ያለው ድህነት በክፋቱ ከአለም ሁለተኛ መሆኑን አስታውቋል። አንደኛውን ደረጃ የያዘችው ምእራብ አፍሪካዊቷ አገር ናይጀር ነች።

ከዚህ ቀደም በስራ ላይ ይውሉ የነበሩ የድህነት መመዘኛዎች፣ የግለሰቦችን የቀን ገቢ ብቻ ከግምት ውስጥ የሚያስገቡ ሲሆኑ፤ አዲሱ መመዘኛ በሰው ልጅ ህይወት ላይ አሉታዊ ተጽእኖ ሊያደርሱ የሚችሉ ዘርፈ ብዙ ጉድለቶችን ከግምት የሚያስገባ ነው። ከነዚህም ውስጥ የትምህርትና የጤና ጥበቃ ሁኔታ፤ እንዲሁም የአጠቃላይ ኑሮ ደረጃን ይለካል። በዚህ መሰረትም፥ ከአስር ኢትዮጵያውያን ዘጠኙ ደሆች ናቸው ሲል ሪፖርቱ ደምድሟል። ጥናቱን ያካሄደው ተቋም ለምርምሩ የተጠቀመው ዳታ ወይም መረጃ የዛሬ አምስት አመት የተሰበሰበ መሆኑንም ገልጿል። በኢትዮጵያ ባለፉት አምስት አመታት፣ በተለይም ከምርጫ 97 በኋላ ዘረኛውና አምባገነናዊው የወያኔ አገዛዝ ስራ ላይ ያዋለውን ሃላፊነት የጎደለው የገንዘብ ፖሊሲ ተከትሎ፣ ቁጥራቸው የማይታወቅ ኢትዮጵያውያን ቀድሞ ከነበረው ወደ ባሰ ድህነት መሸጋገራቸው ይታወቃል።

## የአዲስ አበባ ነዋሪዎች አሁንም በኤሌክትሪክ ሃይል እጥረት ምክንያት እየተንገላቱ መሆናቸው ታወቀ

የወያኔ አገዛዝ የኤሌክትሪክ ሃይልን ለአፈና ተግባራቱ እያባከነ ባለበት ወቅት፣ የአዲስ አበባ ነዋሪዎች በኤሌክትሪክ ሃይል እጥረት ምክንያት መንገላታታቸው እንደቀጠለ ከመዲናይቱ የደረሰን ዘገባ አመልክቷል።

የግንቦት 7 ድምጽ ዘጋቢ ከአዲስ አበባ አጠናቅሮ በላከው መረጃ፥ ሰሞኑን በየቀኑ በአብዛኛው የከተማይቱ ክፍሎች በቀን ቢያንስ ለአራት ሰአታት የመብራት ሃይል ይቋረጣል። ይህ እጥረት በተለይም መብራትን ለንግድ ስራ የሚጠቀሙ ግለሰቦችን እና ሰራተኞቻቸውን ለአላስፈላጊ ወጪ እና ኪሳራ እየዳረገ መሆኑ ታውቋል።

ምንም እንኳ ከሰማንያ በመቶ በላይ የሚሆኑት ኢትዮጵያውያን ቀድሞውኑ የኤሌክትሪክ ሃይል አቅርቦት የማያገኙ እና በዚህ የሃይል መቆራረጥ የማይነኩ ቢሆንም፤ የብዙ የከተማ ነዋሪዎች ኑሮ ግን በኤሌክትሪክ ሃይል አቅርቦት ላይ ጥገኛ መሆኑ ይታወቃል። ፋብሪካዎች፣ ምግብ ቤቶች፣ ቡና ቤቶች፣ ጸጉር አስተካካዮች፣ ሆስፒታሎች እና የመሳሰሉት ድርጅቶች በኤሌክትሪክ ሃይል አቅርቦት ላይ በከፍተኛ ደረጃ ከሚመረኮዙት ውስጥ ይጠቀሳሉ።

የወያኔ አገዛዝ ከውጭ የሚሰራጩ ገለልተኛ የሬድዮ ጣቢያዎችን፤ እንዲሁም በቅርቡ ስራ የጀመረውን የኢትዮጵያ ሳተላይት ቴሌቪዥን ድርጅት ስርጭቶችን ለማፈን ከፍተኛ መጠን ያለው የኤሌክትሪክ ሃይል እንደሚያባክን ከዚህ ቀደም መዘገባችን ይታወሳል።

**የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ**
**የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።**
**በ 7140፣ 7175፣ 7185 KHZ በ 41 ሜትር ባንድ እና በ 6100 KHZ በ 49 ሜትር ባንድ**
ላይ ዘወትር ማክሰኞ፣ ሐሙስ እና ቅዳሜ ከጠዋቱ 3፡00 ሰዓት እስከ 3፡30፤ እንዲሁም ከምሽቱ 2 ሰዓት እስከ 2፡30 የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ በስልክ ወይም በኢሜል በንቅናቀያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።

**ውድ አንባቢዎቻችን**
**ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታሰቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዮን ክፍላችን ዎይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዛችንን እናቀርባለን።** g7radio@ginbot7.org